# ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

14/04/2008

ሕዝብን በዴሞክራሲ እንጂ በጠመንጃ ማንበርከክ አይቻልም!!!!

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ

ላለፉት 25 ዓመታት በዘርና በጎሣ ከፋፍሎ ማንነትክን ላወረደው፣ ታሪክህን ለካደው፣ ለሞት፣ስደትና ሥቃይ የዳረገህን የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ከትከሻህ ላይ አስፈንጥሮ ለመጣል በብዙ ውጣ ውረድ ከፍተኛ መሳናክል አልፎ፣ « የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ የፃነት ንቅናቄ» የተሰኘ ታግሎ አታጋይ ድርጅት በቆራጥ ልጆችህ ፈታውራሪነት ባንተው መሀል፣ በገዛ ልጆችህ በሰኔ 18/10/2007 ዓ ም በይፋ መቋቋሙን ይፋ በማድረግ እንቅስቃሴ መጀመራችንን ይታወሳል።

ላለፉት ስድስት ወራት ለትግሉ አስፈላጊ በሆኑ የአደረጃጀት ስራ ስንሰራ የቆየን ሲሆን አሁን ባለንበት የሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ትግሉን ወደመሬት ላማወረድ ዝግጅታችንን አጠናቀናል።

በመሆኑም ህዝባችን ሃይልና መከታ በማድረግ ወያኔ በሁለገብ ትግል ለማበርከክ ጎዞ መጀመራችንን ለመላው የሀገራችን ህዝብ ስንገልጽ በከፍተኛ የትግል ወኔ ነው።

ፋሽስቱን ወያኔ ከኢትዩጵያ ምድር ጠራርጎ በማጥፋት ዜጎች በአገራቸው በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በወንድማማችነት፣ በመከባበርና በአንድነት የሚኖሩባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ ዳግም ለመፍጠር በሚደረገው ሁለገብ ትግል መላው ህዝባችን ከነፃነት ኃይሎች ጎን በመሰለፍ ታሪካዊ ድርሻውን እንዲወጣ በአክብሮት እንጠይቃለን። ከሰሜን ሀገራችን እስከ ደቡብ ሀገራችን ክፍል ህዝባችን የጀመሩትን የነፃነት ትግል በመደገፍ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ህዝባዊ አመፁን ማቀጣጠል ያስፈልጋል።

አሁን ልዩነቶቻችንን በሙሉ ወደ ጎን ትተን አንድነታችንን በማጠንከር ፋሽስቱን ወያኔ እንቅልፍ መንሳት አለብን። በተለይም ወጣቱ ትውልድ እጥፍ ታሪካዊ አደራ አለበት። በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነፃነት ብሎ ይነሳ።

ከዚህ በኋላ የነፃነት ጉዟችንን ሊያስቆም የሚችል ምንም ምድራዊ ኃይል እንደማይኖር እናምናለን። የአማራ ህዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ ለወሳኙ ፍልሚያ ኃይሉን እያሰባሰበ ስለሚገኝ ህዝባችን ያለምንም ፍርሃት አደባባይ ወጥቶ ወያኔን በቃ ሊል ይገባል።ይህን የህዝብ ብሶት፣ ትዕግስት የወለደው አመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁኖ የሚመራው ማን ነው??? ቀላል የሚመስል አሳሳቢ ጥያቄ እርግጥ ነው በውጪ ሀገር በሳል የኦሮሞ እና አማራ እንዲሁም የመላው ኢትዮጵያ ልሒቃን አቅጣጫ እያስያዙት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ትግል ትዕግስት የወለደው ብሶት ስለሆነ በመላ ኢትዮጵያ እንደ መንፈስ እየተስፋፋ ያለውን የህዝብ የለውጥ ፍላጎት ለድል ላማብቃት የሚያስችል አደረጃጀት ኢትዮጵያ ውስጥ በአስቸኳይ መቋቋም እንዳለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ በጽኑ ያምናል።ከህዝቡ ጎን የሚኖር ግለሰብ ወይም ድርጅት (ድርጅቶች) ኃላፊነቱን ወስደው ሊመሩት የሚገባበት ሰዓት ላይ ደርሰናል፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያን መሠረታዊ ችግሮች ካለው ነባራዊ እውነታ ጋር አገናዝቦ እና አመጣጥኖ ሊመራ የሚችል ቆራጥ እና ጀግና መሪ የግድ ይላል ታግሎ የሚያታግል በሀገር ፍቅር እና በኢትዮጵያ ክብር የማይደራደር icon የሆነ መሪ ድርጅት በእኛ እምነት ይህንን ወቅታዊ ጥያቄ ምላሽ ሊሰጥ የሚችለው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በአንድነት ያሰባሰበው መሪ ድርጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ ነው ብለን እናምናለን!!!

1.በአሁኑ ወቅት ወያኔ እያደረገው ያለውን የመሬት ነጠቃውን በተመለከተ የሚደረገው ተቃውሞ የሚደነቅ ነው ነገር ግን ህወሃት የሃገሪቱን ሀብት በሙሉ ለመቆጣጠር የቆረጠ ቡድን ስለሆነ የሃገሪቱ ዋንኛ ሀብት ደግሞ መሬት በመሆኑ ይህንን ሀብት ለመቆጠጠር የማያደርገው ነገር የለም፥፥ ተቃውሞ ያስቀረዋል ብሎ የሚያስብ ካለ የዋህ ነው፥፥ ስለዚህ ሳይመሽ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚመቸው መንገድ ይደራጅ ፥፥ የግድ በፊት በተደራጁ ፖለቲካ ድርጅቶች መሆን የለበትም በሚመች መንገድ መደራጀት ያስፈልጋል፥፥ ያለ ድርጅት ለውጥ ማምጣት አይቻልም፥፥ የዚህ ሰው ሁሉ መስዋዕትነት በከንቱ መቅረት የለበትም፥፥

2. ብዙ ሰው በጎነደር በኩል ለሱዳን የሚሰጥ መሬት ሲል እንሰማለን ነገር ግን ለሱዳን የሚሰጠው መሬት ከጎንደር ተነስቶ ጋንቤላን አካሎ የሚያልፍ በጣም ሰፊ እና ለም መሬትና የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የግዛት አንድነት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

መላው የሀገራችን ህዝብ እንዳይረባረብበት ወያኔና ጀሌዎቹ ቀን ከለሊት እየሰሩ ይገኛሉ ፥፥ ነገር ግን የጎንደር መሬት እንደሆነ ተደርጎ የሚነዛው ተረት ተረት ወሬ ለጉዳዩ የሚሰጠውን ትኩረት በጣም አናሳ አድርጎታል፥፥የራሳችንን ነጻነትና የሃገራችን ዳር ድበር ለማስከበር ዛሬም እንደትላቱ በአንድነት መነሳት ያለብን ወቅት ላይ ደርሰናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ!!! በህዝብ የተጀመረውን የነጻነት ትግል ለማስቀጠል ከሚደግፉ ማናቸውም ፖለቲካ ድርጅትም ሆነ ሲፊክ ማሃበበጋራት በጋራ በመቀናጀት ትግሉን ለመምራት ዝግጁ መሆናችንን ለመላው

ሀገራችን ህዝብ ለማረጋገጥ እንወዳለን።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄ
የሥራ አመራር ቦርድ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ኢትዮጵያ በጀግኖች በልጆቿ ለዘላለም ትኑር!!!!!!!!!!!!!!!